የግጥም እና የሥነ-ዕሁፍ ፍቅር

ሰላሉዲን የተማሟላ ስብዕና የነበረው ሰው ነበር። ለጀሃድ ጥልቅ ፍቅር ስለነበረው ብዙ ጊዜውን ሰውቶለታል። ነገር ግን የዚያኑ ያህል ሐላል የሆነ ሌላ የሕይወት ድርሻውንም አይዘነጋም ነበር። ኢብን ሸዳድ እንደዘገበው፡- ሰላሉዲን እጅግ በጣም ተግባቢ፣ በመልካም ሥነ-ምግባሮች ያጌጠ፣ ጨዋታ አዋቂ ሰው ነበር። የአረብ የዘር ሃረጎችን እና ጦርነቶቻቸውን በቃሉ ያጠና፣ የግለሰቦቻቸውን የሕይወት ታሪክ፣ ተስፋ እና ሥጋታቸውን ሳይተር ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የፊደሎቻቸውን የዘር ሃረግ ጠቢቅ ያቅየ፣ እንዲሁም በጣም ብዙ ተረቶችን እና አፈታሪኮችን የሚያውቅ ሰው ነበር።

የሰላሉዲን ልዩ ችሎታና አዕምሯዊ አትም ኩሚታያቸው ባህሪዎች መካከል ለግጥም የነበረው አድናቆት ይጠቀሳል። ጥሩ ግጥሞችን ለትርብ ሰዎች በቃሉ ያነበንብላቸው ነበር። ኢብን ኸልካን በግል ታሪኩ ውስጥ ስለሰላሉዲን እንዲህ በማለት ፅፎ ነበር፡- ሰሊሉዲን ጥሩ እና መጥፎ ግጥሞችን ለይቶ የሚያውቅበት መንገድ ነበረው። ብዙ ገጣሚዎች አዲስ የግጥም ሥራዎቻቸውን ወደ ሰላሉዲን በመውሰድ ከፊቱ ያነበንቡለት ነበር። እሱም ታዲያ የወደዳቸውን ግጥሞች በቃሉ ደግሞ የማነብነብ ልማድ ነበረው። ከዚህ በታች ያለው ግጥም ደጋግሞ ያነበንባቸው ከነበሩ ግጥሞች ውስጥ አንዱ ነበር፡-

በጠላቶቹ ተከብቤ በነበረበት ሠዓት
ሌሊቱ አልፎ ሲተርብ ንጋት
ፍትሬን በህልሜ አየኋት. . .
በደስታ ነገንፍ አብትዬ ስከንፍ ስበር
ካጠገቤ የተኙትን ሳነቃቸው ትንሽ ሲቀር
ፍትሬ ለሌሎች ሲገለጥ ሲንደረደር
ዕንቅልፈ አለተ መስል ነቃሁ
ተስፋዎቼ ዕውን እንዲሆኑ ተመኘሁ
ምናለ ባልነቃሁ! ምናለ ባልነቃሁ

"ዋፊያት አል-አያን" የተባለው መፅሐፍ ደራሲ ኢብን አን ሙናጂም በግሮሙ ባነሳው ሃሳብ በጣም ተደስቶ እንደነበር ዕሩል፦

ለምን ሽዝተችውን በተለም ያጠቱሩታል

ምክንያቱም ሽቱት ያስጠላል

ግን ነሮ ወንር ከሥር ሲወጣ የበለጠ ያስተይማል

ለጋ ወጣቶች ሲቀጠፉ ወንር በሃዘን ዕልመት ይለብሳል።

አል-ዓማድ አል-ኣተብ በበኩሉ የሳላሃዲን አፍታሪዎች ሁሉ ግጥም ስንኖች ዕፈው እንደነበር አውስቷል፦

በእነል አብረኸን ባትሆንም

ትርብ ነህ ለልቤ በጣም

በዓይኖቼ አይቼህ ባላውቅም

በልቤ ግን አይቼሃለሁ፤ አይሃለሁ ሁሌም

"ረውደተይን" የተሰኘው መፅሃፍ ደራሲ ሰላሉዲን የዐስማን ኢብን መንኪዘን የግጥም ሥራዎች በጣም ይመድለት እንደነበር እና በጣም ብዙ ግጥሞችን ሽምድዶ በተለያዩ አጋጣሚዎች በቃሉ ይግም ያዘንባቸው እንደነበር ዕሩል። ሰላሉዲን የወንድሙን የተራን ሻህን መሞት የሰማ ጊዜ በጣም አዘኖ እንደነበር እና የተሰማውን ጥልት ሐዘን በግጥም እንደርተር መግለፁን የታሪክ ተመራማሪዎች ዘግበው ነበር። አል-ዓማድ እንደዘገቡት ሰላሉዲን ለንደኛቹ ይፅፋቸው በነበሩ ደብዳቤዎች ውስጥ ደስታውን ወይም መልካም ዜናውን ለንደኛቹ ለመግለፅ የግጥም ስንኖችን ይፅፍ ነበር ብለዋል። ለምሳሌ የሚከተሉት ስንኖች ይጠቀሳሉ፦

ድሮ፤ አያቆምም ነበር እንቡን ማየት

ዛሬ፤ አረካለሁ ደህንነትህን በመስማት

አል-ዓማድ አል-ኣተብ ሰላሉዲን ለሥነ-ዕሁፍ የነበረውን ፍቅር እና ለወሐፊያን የነበረውን ክብር አስመልክቶ እንዲሁም ብዙ ጊዜ አዳዲስ ሥራዎቻቸውን ማየት ይወድ እንደነበር ዕር ነበር። ለግጥም የነበረው

ፍትር ለንድ ነበር በማለት እየሩሳሌምን የተቆጣጠረ ጊዜ ግጥሞች ለህዝብ የሚተርዉበትን መድረክ ማዘጋጀቱን እንደምሳሌ አንስቷል።

ምዕራፍ ሰባት ላይ የተወሰኑ ግጥሞችን ማየታችን ይታወሳል። ግጥም የመተት ልዩ ነህሉት ነበረው። የሚመጡለትን ግጥሞች ደህግ እና ጠንካራ ጎናቸውን በማዝርም ሁኔታ መተንተን ይችል ነበር። አህመድ ኢብን ናሩዳህ ደማስቶ ውስጥ ተወዳጅ የነበረው የሚሸመስ ፍሬ በማያርስበት ደማስቶን እንዲሳበኝ የሚጉጠዉ የግጥም ስንኞችን ለአል-ዓማድ ዕርስት ነበር። በግጥሙ መጀመሪያ ላይ እንዲህ ብሉት ነበር፦

እሱ ሲጋብዝ ጣፋጭ ሚሸመሶችን አጣጥመው እንዲበሉ

ድፍን የደማስቶ ነዋሪዎች ተጠራርተው ይመጣሉ

ይህን ግጥም ለሱልጣኑ ያሳየሁት ጊዜ እኔ ምን ብዬ መልስ እንደሳፍኩለት ጠይቆኝ ነበር በማለት አል-ዓማድ ከዛ በኋላ እንዲህ በማለት ይተርካል፦ በመልሱ የሳፍኩትን ግጥም ሰጠሁት፦

ጣዕማቸውን ለመቅመስ በላ እኛም እንዘርድ

እንገናኝ በራት ሠዓት ካንድ ማዕድ

ሚሸመሶች በዛርች ትጠሉች መሀል ሲታዩ

በብር የተሸፈኑ የወርቅ ኳሶች ይመስላሉ

አል-ዓማድ ሰሰላሑዲን እነዚህን ስንኞች ያነበባለት ጊዜ ገበትጠሉት እና በብር መሳበል ያለው ተመሳስሎ ጥሩ እያደለም፣ ምክንያቱም ትጠሉች አረንጓዴ ሲሆኑ ብር ነጭ ቀለም ነው ያለው። ሁለቱ ደግሞ አያመሳሰሉም።" በማለት ሰላሑዲን አስተያየት ሰጥቶት እንደነበር ጨምሮ ዕሳል። ከዚያም አል-ዓማድ ግጥሙን እንደገና አስተካክሉ ሳፈው፦

ዘሀድ (ተላል ሕይወት መምራት) እና ለጋስነት

ከኅለማዊ ደስታዎች እና ትንጥቂ ነገሮች ራሱን እቅቦ ይኖር ነበር። ተከታዮቹ በሳም የሚያምር ቤት ደማስቶ ውስጥ ሰርተውለት

ነበር ሰላሉዲን ግን ብዙም ሳይደንቀው "እዚህ ቤት ውስጥ ዘላለም እንኖርም። ይህ ቤት ሞቱን ለሚጠይቅ (ሸሒድ መሆንን ከልቡ ለሚመኝ) ሰው ተስማሚ አደደለም። እዚህ የተገኘነው ከሁሉም በላይ የሆነውን አምላክ አላህን ለማገልገል ነው።"[12] ብሏቸው ነበር።

ቢንያልነቱ ወይም በክፍተኛ ሥልጣኑ አያኮራስም ነበር። የገራ ስሜት አደለማውም ነበር። ከተናገራቸው ውስጥ "ገንዘብ እና አቧራ እኒ ዘንድ እኩል ናቸው።" ማለቱ ይጠቀሳል። ሰላሉዲን (አላህ ይዘንለትና) ገንዘብ፣ ትልቅ ቪላ ወይም መኖሪያ ቤት አልነበረውም። ተደም ብለን "አላህን መፍራት እና አምልኮ" በሚለው ነፍስ ውስጥ የሰላሉዲንን ኢማን እና ዒባዳ አስመልክቶ ኢብን ሸዳድ የተናገረውን ማንሳታችን ጠቃሚ ነው።

> ዘነን በተመለከተ፣ ዘነ ማውጣት ግዴታ የሚሆንበት ገቅተኛው የሃብት መጠን እንኳ ሳይኖረው ነበር የሞተው። ለተቸገሩ ሰዎች ስለመመፅወት (ስለ ሰደቃ) ካወራን ደግሞ ገንዘቡን በሙሉ የፈጌረሰው ደሃዎችን በመርዳት፣ የተቸገሩ ሰዎችን በመደገፍ ነበር። ትቶት ያለፈው የሃብት መጠን አርባ ሰባት ዲርሃሞች (የብር ሳንቲሞች) እና አንድ የወርቅ ጁርም (የአንዲት የቲምር ፍሬ የውስጠኛውን ወይም ጠጠሯን ክፍል ያህል መጠን ያላት ወርቅ) ብቻ ነበር። ከዚህ ውጪ ትቶት ያለፈው ሌላ ሃብት፣ ቤት ወይም መሬት፣ የእትክልት ሥፍራ ወይም እርሻ ወይም ሌላ ዓይነት ሃብት አልነበረም።

በታሪክ ካለፉ ትላልቅ ንጉሶች ወይም ትሁት የሚባሉ ገዥዎች ውስጥ ይህን ሱልጣን የሚመስል አንድ መሪ እንኳ አይተዋልን? ወይም አንብበዋልን? ሰላሉዲን ዱንያዊ ደስታዎችን በሙሉ ለአኺራው የሸጠ ድንቅ መሪ ነበር።

---

[12] አህመድ አል-ባያሊ ሐያቱ ሰላሉዲን ገፅ 214

ስለ ሊጋስነት ስንመለከት ደግሞ ሊጢያቂዎች (ለለመኑት ሰዎች) ፍጡም ገንዘብ ከልክለው የማያውቅ፣ የተቸገሩ ሰዎችን እይቶ ማለፍ የማይሆንለት ሰው ነበር። ኢብን ሸዳድ እንዲህ ይላሉ፦

> ከእየሩሳሌም ወደ ደማስቆ ለመንቶሳቱስ ያለበ ጊዜ ብዙ ልዑካኖች ቤቱ ውስጥ ተገኝተው ነበር። ሳንዱቁ (የገንዘብ እና የሌላ ሃብት ማስተመጫ ሳጥን) ውስጥ በቂ ገንዘብ እንደሌለ አውቂ ነበርና ይህንኑ ጉዳይ አላውቂት። ገንዘብ ከሌለ ሳንዱቁ ውስጥ ያሉ ሌሎች ዕቃዎችን እንደሸየ አዘዘኝ እና የፈለገውን እያደረኩለት። ዕቃዎቹ ተሸጠው የተገኘውን ገንዘብ ለልዑካኖቹ አደለ . . ሳላሃዲን በችገር ያሁን በድሎት ጊዜ ሁልጊዜ ሊጋስ ነበር። ይህን ባህረውን የተረዱ አገልጋዮቹ አንዳንድ ጊዜ ለክፉ ቀን ይሆናል በማለት ጥቂት ገንዘብ ይቁተው ያስቀምጡለት ነበር . . . በንግግሩ መሃል ገንዘብን እንደ አፈራ የሚቆጥሩ ሰዎችን ባፈም ማግኘት ይቻላል። ሲል ሰምቻው ነበር። እኔም ይህን የተናገረው አፈሰን አስቦ እንደሆነ አስብ ነበር።

በተለያ ደግሞ ለምሁራን እና ሱፊዮች (መንፈሳዊ ሰዎች) ቦሞ ቸር ነበር። እንዲሁም የቅርብ ሰዎቹ ለእነዚህ ሰዎች ሊጋስ እንዲሆን ያመነር ነበር።አንድ ጊዜ አንድ ምሁር እና ሱፊይ የሆነ ሰው በስተማየ አልፎ ሲሔድ ሱልጣኑ ዘንድ አረፈና ሱልጣኑን አግኝቶ ካነጋረ በኋላ ወዲያውኑ ጉዳውን ተጠለ። ከብዙ ቀናት በኋላ ሰሊሑዲን ስለ ሰውየው ጠየቀ። ሰውየው አሱን አግኝቶ ካነጋረ በኋላ የዚያኑ ቀን መሔዱ ተነገረው። ፊቱ በትህትና ቀላ ቀየሱ። "እንዴት ምንም ነገር ላንሰጠው ያሔዳል?" አለ። ያን ሰውዬ የሚያውቅ አንድ ሠራተኛውን ጠራና ሰውየው ተመልሶ እንዲመጣ የሚጠይቅ መልዕክት አስደሥ ላከው። ሰውየው ጥሪውን አክብሮ መጣ። ሰሊሑዲን በሞቀ ስሜት ተቀብሎ ለብዙ ቀናት በእንግድነት ተንከባከበው፣ ብዙ ጉጽችን እያካ አሟላለተው፣ በመጨረሻ ገንዘብ፣ ሰጦታ እና መንገዋ እንኳን አዘጋጅቶለት ለቤተሰቦቹ እና ለንረቤቶቹ የሚሆን ልብሶችን ሰጥቶ ሸኘው። ሰውየው በጣም ደስ እያለው ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ሰላሑዲን የሆነ ገንዘብ ወይም ሃብት እየመጣ መሆኑን ካወቀ ከእሱ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ለተቸገሩ ሰዎች እና ለወታደሮች እንዲከፋፈል ያደርግ ነበር። የአንድ ተዋጊ ፈረስ በጦር ሜዳ ላይ እንደሞተበት ካወቀ ወንዘቡ ገዙቱ ዘሌላ ይተካለት ነበር። ለራሱ የተለየ ፈረስ ጉሮት አያውቅም፤ ፈረሱን ለወታደሮቹ መስጠት ያዘወትር ነበር፤ ወይም ለሰዎች ስጦታ ለመስጠት ቃል ይገባላቸው ነበር። በዚህ መልኩ በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ ፈረሶችን መስጠቱ ይታወቃል። ብዙ ጊዜ ከላይኑን፤ ከኮሞ ወይም ከሱፍ የተሰሩ ልብሶችን መልበስ ያዘወትር ነበር። ነገር ግን አንድ የሚያስፈልገው ሰው ካገኘ ለዚያ ሰው ስጦታ ያበረክትለት ነበር።[13]

ለዚህ ዛሒድነት እና ለጋስነቱ ካበቱት ውስጣዊ ግፊቶች መካከል አንዱ ራሱን ከጠላት ጋር ለመፋለም የተጋዘዘ የኢስላም ወታደር አድርጎ መመልከቱ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በሦስተኛውም ትዕዝት ሊሞት እንደሚችል ከልቡ ያምን ነበር። ታዲያ ገንዘብ የሚያስፈልጋቸው ብዙ ሰዎች እያሉ ለምን ብሎ ገንዘብ ያጠራቅማል? ሊላው ውስጣዊ ግፊት ደግሞ ለዓለማዊ ደስታዎች፤ ሊሉችን እያዘዘ ለመኖር ወይም ሊሉችን አስፈላጊ ወደሆኑ ቦታዎች ሁሉ እየላከ እሱ ግን ቢተመንግስት ውስጥ ከአገልጋዮቹ ጋር ተቀምጦ የመንደላቀቅ ትንሣት ታሀል ዝንባሌ ያልነበረው ሰው መሆኑ ነበር። ሰላሑዲን ዓውም እንደሊሎች ነገሶች አልነበረም። ከዚህ ይልቅ ጀግና ተፋላሚ እና ፊት አውራሪ ነበርና ብዙ ጊዜውን በጦርነት ሜዳዎች ላይ ነበር ያሳለፈው። አረፍት ያስፈለገው ጊዜ መሬት ይተኛ ነበር ወይም ከድንኳኑ ሥር ተጠልሎ ይቀመጥ ነበር። መስለሞች ድል አደረገ፤ ክብራቸውን መለሱ፤ አንድነት ፈጠሩ ወይም በህብረት አንዳች መልካም ነገር ሠሩ የሚል ዜና የደረሰው ጊዜ ወይም እራሱ የተመለከተ ጊዜ የሚሰማውን የአረፍት ስሜት እና የሚያገኘውን ደስታ የሚተካለት ሌላ ምንም ነገር አልነበረም። ታዲያ እንደዚህ ዓይነቱ ለጋስ እና ድንት መሪ መተት ይገባዋልን? መከሰስ ይኖርበታልን?

---

[13] ፕሮፌሰር ጀማሉዲን አር-ራማዲ ሰላሑዲን ገፅ 96